የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፹፪
አዲስ አበባ ሰኔ ፰ ቀን ፪ሺ፰ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

22nd Year No.82
ADDIS ABABA 15th June, 2016

አዋጅ ቁጥር ፱፻፶፭/፪ሺ፰ ዓ.ም

ለሴቶች የንግድ ስራ ፈጠራ ብቃት ማሳደጊያ ፕሮግራም ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከጣሊያን ሪፐብሊክ መንግስት ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ……………………………………ገጽ ፱ሺ፩፻፪

Proclamation No.955/2016

Government of the Italian Republic Loan Agreement for financing Women Entrepreneurship Development Programme Ratification Proclamation …..………………….. --Page 9102

## አዋጅ ቁጥር ፱፻፶፭/፪ሺ፰

**በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስትና በጣሊያን ሪፐብሊክ መንግስት መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ**

ለሴቶች የንግድ ስራ ፈጠራ ብቃት ማሳደጊያ ፕሮግራም ማስፈፀሚያ የሚውል ፲፭ ሚሊዮን ዩሮ (አስራ አምስት ሚሊዮን ዩሮ) የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስትና በጣሊያን ሪፐብሊክ መንግስት መካከል እ.ኤ.አ. ኖቬምበር ፳ ቀን ፪ሺ፲፭ በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ግንቦት ፳፫ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀፅ ፶፭(፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "ለሴቶች የንግድ ስራ ፈጠራ ብቃት ማሳደጊያ ፕሮግራም ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከጣሊያን ሪፐብሊክ መንግስት ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ

## PROCLAMATION NO.955/2016

**A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE GOVERNMENT OF THE ITALIAN REPUBLIC**

WHEREAS, a Loan Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Italian Republic stipulating that the Government of Italian Republic provide to the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia a loan amount of 15,000,000 Euro (Fifteen Million Euro) for financing Women Entrepreneurship Development Programme was signed in Addis Ababa on the 20th day of November ,2015;

WHEREAS, the House of Peoples' Representative of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Loan Agreement at its session held on the 31st day of May, 2016;

NOW, THERFORE, in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as the "Government of the Italian Republic Loan Agreement for financing Women Entrepreneurship Development Programme Ratification Proclamation No.955/2016".

ር ፱፻፶፫/፪ሺ.፰ ″ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪. <u>የስምምነቱ መፅደቅ</u>

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስትና በጣሊያን ሪፐብሊክ መንግስት መካከል እ.ኤ.አ. ኖቬምበር ፳ ቀን ፪ሺ.፲፮ በአዲስ አበባ የተፈረመው የብድር ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል።

፫. <u>የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሥልጣን</u>

የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፲፭ ሚሊዮን ዩሮ (አስራ አምስት ሚሊዮን ዩሮ) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

፬. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ሰኔ ፰ ቀን ፪ሺ.፰ ዓ.ም**

**ሙላቱ ተሾመ ዶ/ር**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**2. <u>Ratification of the Agreement</u>**

The Loan Agreement signed in Addis Ababa on the 20th day of November 2016 between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Italian Republic is hereby ratified.

**3. <u>Power of the Ministry of Finance and Economic Cooperation</u>**

The Ministry of Finance and Economic Cooperation is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Loan amount of 15,000,000 Euro (Fifteen Million Euro) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

**4. <u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall enter into force on the date of its publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 15th day of June, 2016.**

**MULATU TESHOME (Dr)**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBNLIC OF ETHIOPIA**